
# ዘ ኤምፐረርስ ኤግ (The Emperor's Egg)




## የአር አይ ኤፍ (RIF) መምሪያ ለቤተሰቦች

**ጭብጦች (Themes)፧** እንስሳት፤ ቤተሰብ፤ የህይወት ኡደት

**የመጽሃፉ አጭር መግለጫ (Book Brief)፧** ወንዱ ንጉሠ ነገሥት ፔንግዊን በረዷማ የአንታርክቲክ ክረምት ለሁለት ወራት ያህል ያለ ምግብ ፣ በእንቁላል ላይ ቆሞ የትዳር ጓደኛው ዓሣ ስታጠምድ እሱ እንቁላሉን ያሞቃል። ይህ አስደናቂ ቁርጠኝነት ከተፈጥሮ በጣም ታማኝ አባቶች አንዱ ያደርገዋል።

**ደራሲ፧**
ማርቲን ጀንኪንስ
(Martin Jenkins)

**ሰዓሊ (Illustrator)፧**
ጄን ቻፕማን
(Jane Chapman)

## የንባብ ጊዜ!



**በፊት፧** የታሪኩን ርዕስ ያንብቡና ሽፋኑን ይመልከቱ። ልጅዎን ስለሚያዩት ነገር እና ስለ ፔንግዊን የሚያውቁትን ይጠይቁ።

**በሚያነቡበት ጊዜ፧** በሚያነቡበት ወቅት፤ "የፔንግዊን ወላጆች ለጫጩታቸው ምን እያደረጉ ነው? ለምን?" ብለው ይጠይቁ። እንዲሁም ልጅዎን "ከዚህ በኋላ ምን ይሆናል ብለህ ታስባለህ? ለምን?" ብሎ ትንበያ እንዲሰጥ ይጠይቁት።

**ከንባብ በኋላ፧ ጥያቄዎች ይጠይቁ፧**

- ቤንግዊን ምን ይበላሉ? ወይም የት ነው የሚያገኙንት?
- የፔንግዊን ወላጆች ጫጩታቸውን እንዴት እንደሚንከባከቡ ያብራሩ።
- የፔንግዊን ጫጩት እንዴት ምግብ እንዳገኘ ያብራሩ።

## ሆን ተብሎ የሚደረግ ንግግር (INTENTIONAL TALK)

**ከጽሁፉ ባሻገር ማሰብ (Thinking Beyond the Text)፧** ለአዳዲስ አንባቢዎች ማዳበር የሚገባቸው ጠቃሚ ክህሎት በሚያነቡትና በዙሪያቸው ባለው ዓለም መካከል ግንኙነት መፍጠር ነው። በዚህ መንገድ የራሳቸውን ሃሳብ ወደሚያነቡት ነገር አምጥተው ስለ አንድ ታሪክ ወይም ጽሁፍ የበለጠ ግንዛቤን ያዳብራሉ። እንዲሁም ሃሳባቸውን እና አመለካከታቸውን ለሌሎች እንዲያካፍሉ ይረዳቸዋል።

ዘ ኤምፐረርስ ኤግን (The Emperor's Egg)፤ በሚያነቡበት ወቅት ልጅዎን ስለ ቤተሰብዎ የሚያስታውሳቸውን የታሪኩን ክፍል፣ ወይም ይህን መጽሐፍ ከማንበባቸው በፊት ያዩዋቸውን ነገሮች ሳይቀር እንዲያገኙ ያበረታቱት። ይህ ግንኙነት እንዲፈጥሩ እና መጽሐፉ ከዓለማቸው ጋር እንዴት እንደሚስማማ እንዲመለከቱ እና ከጽሑፉ ጋር ትርጉም እንዲኖራቸው ይረዳቸዋል።

## ተዛማጅ ተግባራት



**እንደፔንግዊን መራመድ** (WADDLE LIKE A PENGUIN)
ቁሳቁሶች፤ በእግርዎ መካከል ማስቀመጥ የሚችሉት ለስላሳ ኳስ ወይም እቃ

ወንዱ ፔንግዊን እንቁላል ከመፈልፈሉ በፊት ለሁለት ወራት ያህል እንዲሞቅ ማድረግ አለበት። እንቁላል የሚወክል ኳስ በእግርዎ ላይ ያስቀምጡ። አባት ፔንግዊን አስመስለው ለመዞር ይሞክሩ፣ ግን እንቁላልዎን አይጣሉ!

## ተጨማሪ ሪሶርሶች (ADDITIONAL RESOURCES)



**በጄን ቻፕማን** (JANE CHAPMAN) **የተጻፉ ሌሎች መጻህፍት**

- ቢር ስኖርስ ኦን (Bear Snores On (2002))
- ዋን ታይኒ ተርትል (One Tiny Turtle (2001))
- ቢግ ቢር ሊትል ቢር (Big Bear Little Bear (2001))

©2025 Reading Is Fundamental

Reading Is Fundamental | Read for Success Early Childhood